ሽ 12

# አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ
# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA


አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ የካቲት ፬ ፪ሺህ፩ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st year No 12
ADDIS ABABA February 11th 2009


ማውጫ


የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ

አዋጅ.......................................ገጽ ፩


**CONTENTS**


A PROCLAMATION TO RE-ESTABLISH THE TECHNICAL AND VOCATIONAL EDUCATION AND TRAINING COLLEGES OF ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT

Proclamation .......................................page 1


### አዋጅ ቁጥር ፲፪/፪ሺህ፩ ዓ.ም
### የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ

ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር መንግስታዊ ተቋም የሆነ መንግስታዊ የሥልጠና ተቋም በአስተዳደሩ ደረጃ ለማቋቋም እንደሚቻል በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አዋጅ ፫፻፺፩/፲፱፻፺፮ የተደነገገውን መነሻ በማድረግ ተቋቁመው በስራ ላይ ካሉት የአስተዳደሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተጨማሪ አዳዲስ ሁለት ኮሌጆችን በማካተት ሰባት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆችን ማቋቋም በማስፈለጉ፣

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ የተደነገገውን መሠረት በማድረግ አደረጃጀትና አሰራራቸውን አስተካክሎ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፩/፲፱፻፺፮ በተደነገገው መሠረት ተጠናክረውና ደረጃ ጠብቀው ትምህርትና ስልጠና የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፲፬(፩) (ሀ)፣ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ አንቀፅ ፰(፪) እና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፩/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፳፮(፪) እንዲሁም አንቀጽ ፪(፲፭)መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

### *Proclamation No 12/2009.*
### *A PROCLAMATION TO RE-ESTABLISH THE TECHNICAL AND VOCATIONAL EDUCATION AND TRAINING COLLEGES OF ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT*

***WHEREAS***, it is found necessary to establish Seven Technical and Vocational Education and Training Colleges which are higher education Institutions of the City Government by adding two new Colleges in addition to the already functioning Colleges that were constituted based on the provisions of the Technical and vocational Education and Training Proclamation No.391/2009 enabling the Government to this effect :

***WHEREAS***, it is found necessary to create conducive conditions by revising their organizational structures and operations in conformity with the Higher Education Proclamation No. 351/2003, so that they conduct education and training in a strengthened and standardized manner as per the provisions of the Technical and vocational Education and Training Proclamation No.391/2004;

***NOW THEREFORE***, the Addis Ababa City Council, pursuant to Article 14(1) (a)of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No.361/2003 (as Amended), Article 8(2) of the Higher Education Proclamation No. 351/2003 and Articles 26(2) as well as Article 2(15) of the Technical and Vocational Education and Training Proclamation No.391/2004, has hereby promulgated this Proclamation as follows :


አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 8.80



www.chilot.me

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፪/፪ሺህ፩ ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠዉ በስተቀር፣

፩ «አስተዳደር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው::

፪ «ምክር ቤት» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ነዉ::

፫ «ከንቲባ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ነው::

፬ «ካቢኔ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው::

፭ «ኤጀንሲ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ነው::

፮ «የአካዳሚክና ሥልጠና ሠራተኛ» ማለት በማስተማርና በማስልጠን ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሰማራ የኮሌጁ ሠራተኛ ነው::

፯ «የአስተዳደር ሠራተኛ» ማለት የአካዳሚክና ሥልጠና ሠራተኛ ያልሆነ የኮሌጁ ሠራተኛ ነው፣

፰ «አካዳሚክ ኮሚሽን» ማለት የኮሌጁ ዋናና ምክትል ዲኖች፣ የዲፓርትመንቶችና የጽህፈት ቤት ኃላፊዎች፣ የመምህራን ተወካዮች፣ የተማሪዎች መማክርትና የሴቶች ተወካዮችን ያቀፈ በየኮሌጁ የሚቋቋም ተጠሪነቱ ለዲኑ የሆነ ከትምህርትና ስልጠና ጋር በተያያዘ ቴክኒካዊ በሆነ ልዩ ልዩ የማማከርና የማመቻቸት ተግባራትን የሚያከናውን አካል ነው::

፱ «ኮሌጅ» ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከደረጃ ፩-፭ እና ሌሎች የገበያ ፍላጐት መሠረት ያደረጉ አጫጭር ሥልጠናዎችን የሚሰጥ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ሕጋዊ የሥልጠና ኮሌጅ ማለት ነው::

፲ «ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር» ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስትር ወይም የትምህርት ሚኒስቴር ነው::



## PART ONE
## GENERAL

*1. Short Title*

This Proclamation may be sited as « A Proclamation to Re-Establish the Technical and Vocational Education and Training Colleges of Addis Ababa City Government proclamation No. 12/2009 »

*2. Definition*

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:-

1. "Government'' means Addis Ababa City Government;
2. "Council" means the Council of Addis Ababa City Government
3. "Mayor" means the Addis Ababa City Mayor.
4. "Cabinet'' means the Cabinet of Addis Ababa City Government".
5. "Agency'' means the Technical and Vocational Education and Training Agency of Addis Ababa City Government;
6. "Academic and Training Staff'' means an employee of the College engaged in the work of teaching and training or research activity;
7. "Administrative Staff'' means an employee of the College which is not an academic and training staff.
8. "Academic Commission" means an organ which consists of the dean and the deputy deans, heads of departments and offices, representative of lecturers, representative of students council and women, established in each college, accountable to the dean, carry out various technical advisory and facilitating activities.
9. " College'' means any legal governmental or non-governmental institution that provides training from level 1-5 and offers other short term trainings based on the market demand.
10. " Minister or Ministry" means the Minister of the Education or Ministry of Education respectively.

## ክፍል ሁለት

## የኮሌጆች መቋቋም፣አደረጃጀትና ዓላማ

### ፫. መቋቋም

፩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ሀ) እንጦጦ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ /ከዚህ በኋላ «ኮሌጅ» ተብሎ የሚጠራ/ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመሆን በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

ለ) ጀኔራል ዊንጌት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ /ከዚህ በኋላ «ኮሌጅ» ተብሎ የሚጠራ /ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመሆን በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

ሐ) አዲስ አበባ ተግባረዕድ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ/ ከዚህ በኋላ «ኮሌጅ» ተብሎ የሚጠራ/ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመሆን በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

መ) ንፋስ ስልክ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ /ከዚህ በኋላ «ኮሌጅ» ተብሎ የሚጠራ /ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመሆን በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

ሠ) ምሥራቅ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ /ከዚህ በኋላ «ኮሌጅ» ተብሎ የሚጠራ /ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመሆን በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

ረ/ አቃቂ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ /ከዚህ በኋላ «ኮሌጅ» ተብሎ የሚጠራ/ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመሆን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

## PART TWO

## Establishment, Organization and objective Colleges

### 3. *Establishment*

1 .The Addis Ababa City Government: -

a) Entoto Technical and Vocational Education and Training College (here in after referred to as the "College") is hereby re-established by these Proclamation as higher education institutions of the City Government having its own legal personality.

b) General winget Technical and vocational Education and Training college (here in after referred to as the "College") is hereby Re-established by this Proclamation as higher education institution of the City Government having its own legal personality.

c) Addis Ababa Tegbareid Technical and Vocational Education and Training Collage (here in after referred to as the "Collage") is hereby Re-established by these Proclamation as higher education institution of the city Government having its own legal personality.

d) Nefas Silk Technical and Vocational Education and Training College (here in after referred to as the "college"') is hereby Re-established by these Proclamation as higher education institution of the City Government having its own legal personality.

e) Misrak Technical and vocational Education and Training College (here in after referred to as the "College") is hereby Re-established by these Proclamation as higher education institution of the City Government having its own legal personality.

f/ Akaki Technical and Vocational Education and Training College (here in after referred to as the "College") is here by e.tablished by these Proclamation as a higher education institution of the City Government having its own legal personality.

ሰ/ ኢትዮ ቻይና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ/ ከዚህ በኋላ «ኮሌጅ» ተብሎ የሚጠራ/ ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመሆን ከዚሀ በኋላ «ኮሌጅ» ተብሎ የሚጠራ ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመሆን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪ የእያንዳንዱ ኮሌጅ ተጠሪነት በቀጥታ ለኤጀንሲው ይሆናል፡፡

፬. አደረጃጀት

፩ እያንዳንዱ ኮሌጅ፡-

ሀ/ የራሱ የአስተዳደር ቦርድ (ከዚህ በኋላ ቦርድ ተብሎ የሚጠራ)፣

ለ/ ዲን፣

ሐ/ ሁለት ምክትል ዲኖች፣

መ/ አካዳሚክ ኮሚሽን፣

ሠ/ ጽህፈት ቤትና ለሥራው የሚያስፈልጉ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡

፪ እያንዳንዱ ኮሌጅ በአካዳሚክ ዘርፉ በኩል፣

ሀ/ የሥልጠና ዲፖርትመንቶች፣

ለ/ የዲፖርትመንት ጉባዔዎች እና

ሐ/ የምርምር ክፍሎች ይኖሩታል፡፡

፫. እያንዳንዱ ኮሌጅ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ውስጣዊ አካላትና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፭. ዓላማ

እያንዳንዱ ኮሌጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

፩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የመስጠት እና ምርምር የማካሄድ፣

፪ ኢንቨስትመንትን፣ የሥራ ፈጠራን እና የሥራ ውጤታማነትን ከማበረታታትና ከማጐልበት አኳያ ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት እንዲሁም ለሌሎች የባለድርሻ አካላት ተገቢውን የምክርና የድጋፍ አገልግሎት መስጠት

፫ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የፈጠራ ማዕከል በመሆን ድጋፍ መስጠት፣

ክፍል ሶስት

የኮሌጆች ሥልጣንና ተግባራት

፮ የኮሌጆች ሥልጣንና ተግባር

እያንዳንዱ ኮሌጅ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-



g/ Ethio- China Polytechnic College (here in after referred to as the 'collage' is hereby established by these proclamation as a higher education institution of the City Government having its own legal Personality.

2. Each college shall directly be accountable to the Agency.

4. ***Organization***

1 Each College shall have:

(a) Its own administrative board (hereinafter referred to as the "Board");

(b) Dean;

(c) Two Deputy Deans;

(d) An Academic Commission;

(e) Office and other necessary departments for the activities;

2. Each college shall in its academic section have:-

(a) Training Departments;

(b) Department Assembles; and

(c) Research Sections.

3. Each College shall have other necessary internal organs and staff.

5. ***Objectives***

Each College shall have the following objectives:

1. providing Technical and Vocational Education and Training, conducting research,
2. rendering proper consultancy and support services to Micro and Small Enterprises and other stake holders in encouraging and strengthening investment, job creation and job effectiveness.
3. providing support being a center for technology transfer and creativity.

***PART THREE***

***Power and Functions of the Colleges***

6. ***Powers and Duties of the College***

Each College shall have the following powers and functions;

www.chilot.me

፩ በአገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጂ እና በአስተዳደሩ ፍላጐት መሠረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የምርምርና የምክር አገልግሎት መርሃ ግብሮችን ይቀይሳል፣ ሥራ ላይ ያውላል፡፡

፪ በሚኒስቴሩ በሚወጣው የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ነጥብ መሠረት የአስተዳደሩ ነዋሪ የሆኑ ተማሪዎችን ይቀበላል፡፡ እንዲሁም በኤጀንሲው በሚሰጠው አመራር መሠረት በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ነዋሪ የሆኑ አመልካቾችን ሊቀበል ይችላል፡፡

፫ ለትምህርትና ሥልጠናው ተመጣጣኝ የሆነ የምሥክር ወረቀት እንዲሁም ለከፍተኛ ውጤትና አስተዋጽኦ የሚገባ አካዳሚክ ሜዳሊያ ሽልማትና ማዕረግ ይሰጣል፡፡

፬ የትምህርት፣ የጥናትና የምርምር ክፍሎችን ያቋቁማል፡፡

፭ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገሮች ካሉ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር ግንኙነት ይመሠርታል፡፡

፮ የተለያዩ ትምህርታዊ ሴሚናሮችን፣ ወርክሾፖችን ሲምፖዚየሞችንና ኤግዚቢሽኖችን ያካሂዳል፤

፯ ልዩ ልዩ ስልቶችን በመቀየስ የራሱን የውስጥ ገቢ ያዳብራል እንደዚሁም እነዚህን ገቢዎች በቦርዱ እያስፀደቀ መጠቀም ይችላል፡፡

፰ ለሚሰጠው ሙያዊ አገልግሎት ተገቢውን ዋጋ ያስከፍላል፡፡

፱ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ያስተዳድራል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ መክሰስ ወይም መከሰስ ይችላል፡፡

፲ መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በሚደረጉ ትብብሮች ኮሌጁ ትምህርትና ስልጠና መስጠት የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ያስፋፋል፡፡

፲፩ ተገቢውን በጀት በማስፈቀድ የአካዳሚክና የአስተ ዳደር ሠራተኞችን አግባብ ባለው ህግ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፡፡

፲፪ ኮሌጁ የቴኪኖሎጂ ሽግግርና የፈጠራ ማእከል እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፲፫ በገበያ ፍላጎት የሚመራ ሥልጠና እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

፲፬ ለኮሌጁ አሰልጣኞች ተከታታይ ሥልጠና ይሰ ጣል፤የኮሌጁን ሥራ አስፈጻሚ አካላትና ባለሙ ያዎች አቅም ለመገንባት ስልጠና ያካሂዳል፡፡



1. It shall formulate and implement Technical and Vocational Education and Training, research and consultation service in line with needs of the Government, the National Education and Training Policy and the National Technical and Vocational Education and Training Strategy.
2. It shall admit students who are residents of Addis Ababa according to the higher education entrance criteria set by the Ministry. like wise it may admit applicants from other parts of the country in line with the direction given to it by the Agency;
3. It shall reward certificates equivalent to the education and training it offers as well as medals, prizes and titles for higher achievements and meritorious contributions.
4. It shall establish academic, study and research departments
5. It shall establish relations with counter part domestic and foreign institutions having similar objectives.
6. It shall conduct various educational seminars, workshops, symposiums and exhibitions.
7. It shall formulate various mechanisms to develop its own internal incomes and may make use of such incomes upon approval by the Board.
8. It shall collect appropriate charges in return for the professional services it renders.
9. It may own and manage property, conclude contracts, and sue or may be sued in its own name.
10. It shall extend conditions in which the College can provide education and training through cooperation arrangements to be made with Governmental and non governmental organizations.
11. It shall employ, manage and dismiss the employees of academic and administrative staff according to the relevant law up on approval of appropriate budget.
12. It shall make the College to be the centre of transfer and invention of technology,
13. It shall conduct market oriented training. are conducted .
14. It shall render continuous trainings to trainers; It shall conduct training to build the capacity of executive and build the capacity of executive bodies and other Professionals of the Collage

www.chilot.me

፲፭ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ጋር ለማስተሳሰር ከአጋር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፤ እንዲሁም የተለያዩ አጫጭር የሙያ ሥልጠናዎች በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለተደራጁና ለሚደራጁ ወጣቶች ይሰጣል።

፲፮ የተግባር አፈፃፀሙንና የበጀት አጠቃቀሙን የየሩብ እና ዓመታዊ ሪፖርት ለኤጀንሲው ያቀርባል፡

፲፯ ዓላማውን የሚያዳብሩና የሚያራምዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል።

## ክፍል አራት

## ስለልዩ ልዩ አካላት ሥልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀት

፯. የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩. እያንዳንዱን ኮሌጅ በበላነት ይመራል፤ ያስተዳድራል።

፪. ከቦርዱ የቀረበለትን የእያንዳንዱን ኮሌጅ ዕቅድና በጀት መርምሮ ይወስናል፤ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል።

፫. የዲኖችንና የም/ዲኖችን የትምህርት ዝግጅት የሥራ ልምድና ብቃትን በመገምገምና የየኮሌጁ ቦርድ አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግ ለከተማው ከንቲባ አቅርቦ እንዲሾሙ ያደርጋል።

፬. በኤጀንሲዉ አዋጅ ላይ የተገለፁ ሌሎች ስልጣንና ኃላፊነቶችን ይተገብራል።

፰. የቦርድ አመሠራረት

፩ እያንዳንዱ ኮሌጅ ከተለያዩ አካላት የተውጣጡ ቁጥራቸው ከ፯-፱ የሚደርስ አባላት ያሉት አንድ ቦርድ ይኖረዋል።

፪ የእያንዳንዱ ቦርድ አባላት ጥንቅር የሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) በከንቲባው የሚሰየም ---------- ሰብሳቢ፣



15. It shall work in coordination with stake holder organizations to integrate technical and vocational trainings with Micro and small Enterprise; likewise, it shall render various tailor made short term trainings for those who organized and/or would be organized in Micro and small Enterprise.

16. It shall submit utilization of quarterly and annual report performance and budget.

17. It shall carry out other related activities that enhance and promote its objectives

## *PART FOUR*

## *Power, Function and Organization of various Bodies*

7. ***Powers and Functions of the Agency***

The Agency shall have the following power and functions to:-

1. It shall supervise and manage each College.
2. It shall examine and determine the plans and budget of each College submitted by the board and it shall control their implementation.
3. It shall propose the appointment of the dean and deputy deans of each Collage by the City Mayor by evaluating their academic qualifications, work experiences and over all competence on its own and considering the recommendations of the respective Board.
4. It shall perform other power and functions stated on the proclamation of Agency.

8. ***Establishment of the Board***

1. Each college shall have a board having 7-9 members recruited from various organs.
2. The board shall consist of the following members:-

(a) a person who shall be designated by the Mayor ...................... chair person.

ለ) የኤጀንሲው ተወካይ ------------------ አባል፣

ሐ) የአስተዳደሩ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተወካይ ---------------- አባል፣

መ) ከጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት ኤጀንሲ ተወካይ-----------አባል

ሠ) የኮሌጁ ዲን ---------------- አባልና ፀሐፊ፣

ረ) ከትምህርት ቢሮ አንድ ተወካይ -- አባል

ሰ) ከቀጣሪ ድርጅቶች / ኢንዱስትሪዎች ፣ ካምፓኒዎች እና የንግድ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች/ አንድ ተወካይ ------ አባል

ሸ. በከንቲባው የሚሰየሙ ሁለት ተወካዮች----- አባል

፫ የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ፫ ዓመት ይሆናል፣ ሆኖም ማንኛውም አባል እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ ሊሰየም ይችላል፡፡

**፱. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርዱ ተጠሪነቱ ለኤጀንሲው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ የኮሌጁ የበላይ ኃላፊ ሆኖ ይሰራል፡፡

፪ አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ለመንግስታዊ ተቋም የተሰጠውን የትምህርት ኃላፊነት ያልተወጣ ወይም የዲስፕሊን ጥፋት የፈፀመ የኮሌጁ የሥራ ኃላፊ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፣ በኤጀንሲው በኩል ለከንቲባው አቅርቦ ከኃላፊነት ያሰናብታል፡፡

፫ በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኮሌጁን አደረጃጀት፣ ፖሊሲዎች፣ አስተዳደራዊ የውስጥ ደንቦችና መርሐ ግብሮች ያፀድቃል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፡፡



(b) a representative of the Agency ------member

(c) a representative of the Finance and Economic Development Bureau of the City --------------- member

(d) a representative Micro and Small Scale enterprises development Agency. --- member

(e) The Dean of the College----- member and secretary.

(f) Bureau of Education ---------------member.

(g) a representative of employers(Industries, companies and Service giving organization)- --- member .

(h) Two Representatives designated by the Mayor ------------------------- Members.

3. The term office of Board member shall be 3 years. However, any board member may be designated for only one more additional term of office.

**9. *Powers and function of the Board***

The Board shall be accountable to the Agency, it shall have the following powers and functions:

1. It shall be the chief administrator of the college
2. Without prejudice to the applicability of other relevant laws; It shall take disciplinary action against official of the college who fails to discharge his academic duties or disciplinary offence; It shall submit for dismissal to the Mayor through the Agency, and present to the mayor through the Agency, for dismissal.
3. With out prejudice to the provisions of this Proclamation, it shall approve the organizational structure, policies and internal Administrative regulations and programs of the college and follow up their implementation.

፬ በኮሌጁ ዲን የሚቀርብለትን ዕቅድ፣ በጀት እና የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት መርምሮ ተገቢውን በመፈጸም ለኤጀንሲው ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

፭ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት የኮሌጁን ኦዲተር ይሰይማል፤የአገልግሎት ክፍያውን ይወስናል።

፮ የመንግስት ሠራተኞች ሕግ መሰረታዊ መርሆዎችን በመንተራስ የኮሌጁ አካዳሚክ፣ የምርምርና የስልጠና ሠራተኞች ቅጥር፣ ዕድገት፣ ዲስፕሊን፣ ደመወዝ፣ አበል፣ ምንዳና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን የሚመለከት መነሻ ሀሳቦችን በማስጠናት የውሳኔ ሀሳብ ለኤጀንሲው ያቀርባል፣ ሲወሰንም አፈጻጸሙን ይከታተላል።

፯ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የኮሌጁ የፋይናንስ ሂሳብ መዝገብ መግለጫዎች በማስቀረብ እንዲመረመሩ ያደርጋል።

፰ የኮሌጁን ስትራቴጂካዊ የልማት ዕቅድ ያፀድቃል።

፱ የኮሌጁ ዓላማዎች ተፈጻሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ ኮሌጁ በአሳታፊነት፣ በግልፅነትና በተጠያቂነት ላይ ተመስርቶ ተግባሩን ማከናወኑን ይቆጣጠራል።

፲ ዝርዝሩ በኮሌጁ የውስጥ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በኮሌጁ ወይም በአንድ ክፍሉ በተሰጠ ውሣኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን መርምሮ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል።

፲፩ ኮሌጁ ከአገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር የሚያደርጋቸውን ትምህርትና ስልጠና ነክ ስምምነቶች እንደአስፈላጊነቱ ያፀድቃል።

4. It shall examine and make appropriate the plan, budget and performance reports which is submitted to it by the Dean of the college and submit the same to the Agency; it shall also follow up the implementation thereof up on approval.

5. It shall designate an auditor to the College in accordance with relevant law and determine service payment for the same.

6. It shall forward to the Agency recommendations regarding the employment, promotion, discipline, salary, allowances, wages and other benefits of the academic, research and training staff of the College having made sure that a study is undertaken on the basis of the basic principles of Civil service law, and follow up the implementation thereof up on approval.

7. It shall cause the submission and investigation of financial record statements of the college, whenever it is necessary.

8. It shall approve the strategic development plan of the college.

9. It shall ensure the achievement of the objectives of the college; it shall ensure that the college has carried out its activities on the basis of principles of participation, transparency and accountability.

10 It shall examine and give final administrative decision on the complaints to be logged against the decision of the College or its departments, provided that the particulars thereof shall be determined by internal regulations of the college.

11. It shall approve, as may be necessary, agreements that the college concludes with local and foreign high education institutions relating to education. and training.

www.chilot.me

፲፪ የኮሌጁን መለያ ምልክት ወይም አርማ ይወስናል::

፲፫ የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት እና ውስጠ ደንብ ያወጣል::

፲፬ የሌክቸረር እና ከሌክቸረር በላይ ያለ ማዕረግን ያፀድቃል::

፲፭ ኮሌጁ ከትምህርትና ስልጠና ጋር በተያያዘ የሚያስከፍላቸውን ክፍያዎች በማስጠናት የውሳኔ ሀሳብ ለኤጀንሲው ያቀርባል::

፲፮ የኮሌጁ የትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር ኘሮግራም ከሐገርና ከአዲስ አበባ ሕዝብ ጥቅሞች አንፃር መዘጋጀቱንና በዓላማዎቹ መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል::

## ፲. የቦርድ አባላት ተጠያቂነትና አበል

፩. ቦርዱ የሚሰጠው ውሣኔ ሕግን በሚጥስበት ጊዜ ለሚያስከትለው ኃላፊነት በውሣኔው የተሳተፈ እያንዳንዱ የቦርድ አባል በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናል::

፪. እያንዳንዱ የቦርድ አባል በኮሌጁ አበል ይከፈለዋል :: የአበሉ መጠን በካቢኔው ይወሰናል::

## ፲፩ <u>የቦርዱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ቦርዱ:-</u>

፩ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ሰብሳቢው ሲጠራ በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል::

፪ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል::

፫ ውሣኔውን በአብላጫ ድምጽ ያስተላልፋል:: ሆኖም ድምጽ እኩል ከተከፈለ የሰብሳቢው ድምጽ ያለበት ወገን የቦርዱ ውሣኔ ይሆናል:: እንዲሁም ማንኛውም የውሣኔ ልዩነት ይመዘገባል::

፬ በዚህ አንቀጽ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፣ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል::

12. It shall determine the identification mark or emblem of the College.

13. It shall issue its own meeting procedures and internal regulations.

14. It shall approve a title of lecturer and higher than lecturer

15. It shall forward to the Agency recommendations regarding payments to be charged by the college in relation to education and training ascertaining that studies are undertaken there upon.

16. It shall ensure that education; training and research programs of the college are formulated and implemented in view of the interests of the people of the country and Addis Ababa as well as their implementation as per the objectives of the College.

## 10. *Liabilities and Allowances of Board members*

1. Each member who has voted for it shall be jointly and severally liable to what such a decision entails where the decision of the Board violates a law.

2. Each member of the board shall be paid allowance by the College; and the amount of such allowance shall be determined by the Cabinet.

## 11 *Meeting procedures of the Board*

**The Board Shall:-**

1. meet once in a month. However, the chair person calls for a meeting at any time when emergency so requires

2. have a quorum when more than half of its members are present.

3. pass decisions by a majority vote when votes are in tie, the decision of the Board shall be the decision of the group which the chair person supports. Any dissenting opinion shall be recorded.

4. without prejudice to the provisions set out under this Article, the board may issue its own meeting procedures.

www.chilot.me

፲፪ ስለ እያንዳንዱ ኮሌጅ ዲንና ምክትል ዲኖች ሹመትና ተጠሪነት

፩ የእያንዳንዱ ኮሌጅ ዲን እና ምክትል ዲኖች በኤጀንሲው አቅራቢነት በከንቲባው በብቃታቸው የሚሰየሙ ሲሆን ተጠሪነታቸውም ለኤጀንሲው ይሆናል፡፡

፪ የዲኖችና የምክትል ዲኖች የሹመት ጊዜ ሶስት ዓመት ሆኖ፣ ውጤትን መሠረት በማድረግ ለሶስት ዓመት እንደአስፈላጊነቱ ሊራዘም ይችላል፡፡ ሆኖም ተፈላጊ ውጤት በተመደ በበት ዓመታት ውስጥ ካላስመዘገበ ወይም በሥነ ምግባር ጉድለት በማንኛውም ጊዜ ሹመቱ ሊነሳ ይችላል፡፡

፫ በሥራ አፈፃፀም ብቃት ማነስ ወይም በሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት የኮሌጅ ዲንን ወይም ምክትል ዲኖቹን ከኃላፊነት ማሰናበት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ኤጀንሲው ከሥራ አግዶ ለከንቲባዉ ውሣኔ እንዲሰጥበት ከአስተያየት ጋር ያስተላልፋል፡፡

፲፫. የዲኑ ሥልጣንና ሀላፊነት

ዲኑ የኮሌጁ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ሀላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩. በዚህ አዋጅና ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር መሠረት የኮሌጁን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣

፪. የኤጀንሲውና የቦርዱ ውሣኔዎችና መመሪያዎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

፫. የአካዳሚክና ሥልጠና ሠራተኞችን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይቀጥራል ወይም መቀጠራቸውን ያረጋግጣል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

፬. የአስተዳደር ሠራተኞችን በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፡፡

፭. የኮሌጁን ገቢ የኮሌጁን ዓላማ ለማስፈፀም ስራ ላይ ያውላል፡፡

፮. ቦርዱ ባወጣው መመሪያ እና በሌሎች ህጎች መሰረት እንደየአግባቡ በኮሌጁ ሠራተኞች ወይም ተማሪዎች ላይ የሚቀርብ የዲሲፒሊን ጉዳይን አይቶ ይወስናል፡፡

12. ***Appointment and Accountability of the Dean and Deputy-Deans of each College***

1. The Dean and the deputy -Deans of each college shall be appointed based on merit by the City Mayor up on the recommendation of the Agency and shall be accountable to the Agency.
2. The Dean and the Deputy Deans of each college shall be appointed for an other three years. The appointment may be extended for three years depending up on their respective performance. However, the appointment can be terminated at any time based on performance results or ethical problem.
3. Where the Agency finds it necessary to dismiss the Dean or deputy-Deans of a College from office on acount of incompetence or breach of professional ethics. It shall, with its recommendation, refer the matter to the Mayor after having suspended such a Dean or deputy-Dean from office.

13. ***Powers and Responsibilities of a Dean***

***The*** **Dean of a college shall be the chief executive of the College and he shall:-**

1. direct, administer and control the activities of the College pursuant to this Proclamation and the general directions to be given to him by the Board.
2. ensure that the decisions and guidelines of the Agency and the Board are properly implemented;
3. employ, administer and dismiss or ensure the employment of academic and training staff in accordance with the guidelines issued by the Board.
4. employ, administer and dismiss administrative staff in accordance with the civil service law;
5. utilize the incomes of the college to achieve the objectives thereof.
6. examine and decide on disciplinary cases of employees and students of the college in accordance with guidelines issued by the Boards and other laws as the case may be.

www.chilot.me

፯. የአካዳሚክ ኮሚሽኑን ሃሳብ ግምት ውስጥ በማስገባት የኮሌጁን ስትራቴጂያዊና የልማት ዕቅድ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

፰. የኮሌጁን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት በዚህ አዋጅ መሠረት በየደረጃው እንዲዘጋጅ አድርጐ በቦርዱ ሲታዘዝ ለኤጀንሲው ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

፱. የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፱ ንዑስ አንቀፅ (፲፩) እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በኮሌጁ ስም የሚደረጉ ውሎችን ይፈርማል፤

፲. በአስተዳደሩ የፋይናንስ አስተዳደር ህጎች መሠረት በኮሌጁ ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፤ ያንቀሳቅሳል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውክልና ይሰጣል፤

፲፩. ኮሌጁን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፡፡

፲፪. ለኮሌጁ ሥራ ቀልጣፋነትና ስኬታማነት በሚያመች መጠን ከኃላፊነቱ በመቀነስ እንደአስፈላጊነቱ ለምክትል ዲንና ለሥራ ክፍል ኃላፊዎች በውክልና ይሰጣል፡፡

፲፫. ከተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የትብብር ሥልጠና እንዲሰጥ ኮሌጁን በመወከል ይፈራረማል፡፡

፲፬. የኮሌጁን የሥራ አፈፃፀም ሂደትና የበጀት አጠቃቀም በቦርዱ በማስጸደቅ ለኤጀንሲው በየሩብ ዓመቱ እና በየዓመቱ የግምገማ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፲፭. የኮሌጁ የመማር ማስተማር ሂደት፣ እንዲሁም የጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚጠናከሩ በትን ስልት ይቀይሳል፣ ቦርዱን በማስወሰን ለኤጀንሲው ቀርቦ ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል፣

7. prepare and submit to the Board the strategic and development plan of the college taking into consideration the recommendations of the Academic Commission.

8. ensure the preparation of yearly action plans and budget proposals of the Collage at every level pursuant to this Proclamation and shall submit them to the Agency upon the direction of the Board. He shall also ensure the implementation of same upon approval.

9. without prejudice to Article 9 Sub Article (11) 0f this Proclamation he shall Sign on contracts made in the name of the college.

10. open and operate bank accounts in the name of the College in accordance with the Finance administration laws of the Government; Delegate whenever necessary.

11. represent the College in its all dealings with third parties.

12. delegate part of his duties to deputy-deans and other heads of different sections to the extent necessary for the expediency and effective performance of the college.

13. sign, on behalf of the College, agreements that enable to provide trainings in cooperation with various Governmental and non Governmental organizations.

14. submit to the Agency quarterly and yearly evaluation reports concerning the progress of the performance and budget utilization of the College after having secured the approval of the Board ;

15. devise strategies by which the teaching-learning process as well as study and research activities of the College may be developed and strengthened secure the decision of the Board; there upon and implement upon approval by the Agency.

፲፮. በቦርዱና በኤጀንሲው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮች ያከናውናል፣

፲፬. የየኮሌጁ የአካዳሚክ፣ የሥልጠናና ምርምር ምክትል ዲን ሥልጣንና ኃላፊነት፡-

የአካዳሚክ፣ የሥልጠናና የምርምር ምክትል ዲን ተጠሪነቱ ለዲኑ ሆኖ፣

፩ የኮሌጁን አካዳሚክና ሥልጠና ተግባራት በሚመለከት ዲኑን ያማክራል፣ይረዳል፡፡

፪ የኤጀንሲውን፣ የአካዳሚክና ሥልጠና ኮሚሽኑ ውሣኔዎች እንዲሁም የአካዳሚክና ሥልጠና መመሪያዎች ደንቦች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡

፫ የትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር ተግባሮችን ዕቅድ ዝግጅትን ያስተባብራል፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡

፬ ኮሌጁ የሚሰጣቸው የሥልጠና ሞጁሎች አካዳሚክና ሥልጠና ኮሚሽኑ ባፀደቀው የትምህርት ካላንደርና ፕሮግራሞች መሠረት መካሄዳቸውን ያረጋግጣል፣ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፭ የትምህርትና ሥልጠና ሂደቱን ለማዳበር አስፈላጊ ድጋፎችና አገልግሎቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፣ ስለአፈፃፀሙ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፮ የኮሌጁን የማማከር አገልግሎት ሥራዎች ያስተባብራል ፣ በአግባቡ መከናወኑን ያረጋግ ጣል ፣ ስለአፈፃፀሙም በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፯. የኮሌጁ ዲን በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሠራል፣

፰. በኤጀንሲው፣ በዲኑና በአካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

፲፭. የየኮሌጁ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን ሥልጣንና ሀላፊነት

የአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን ተጠሪነቱ ለዲኑ ሆኖ፣



16. carry out other related tasks assigned to him by the Board and the Agency.

14. ***Powers and Responsibilities of the Deputy -Dean of Academic, Training and Research of Each College***

The Deputy-dean of Academic, Training and Research, being accountable to the Dean, he shall:-

1. advise and assist the Dean in respect of the academic and training activities of the College.
2. ensure the implementation of the decisions of the Agency, the Academic and Training Commission as well as academic and training rules and regulations.
3. coordinate the preparation of the plan of academic, training and research activities and shall ensure its implementation when approved.
4. ensure that the training modules that the College offers are conducted in conformity with the academic and training calendar and programs approved by the Academic and Training Commission and report the execution thereof.
5. ensure that facilities and services necessary to enhance the education and training process are available; and he shall submit performance reports there about.
6. co-ordinate consultancy activities of the College, ensure their proper implementation and submit report periodically about the performance thereof.
7. act on behalf of the Dean in his absence;
8. perform other activities assigned to him by the Agency, the Academic Dean, and the Commission.

15. ***Powers and Responsibilities of the Deputy -Dean of Each Administration and Development College.***

The Deputy-Dean of Administration and Development. Being accountable to the Dean of the College shall:-

፩ የኮሌጁን የአስተዳደርና ፋይናንስ ተግባሮች ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡

፪ ኮሌጁን ለማሳደግ የታለመ የልማት ሥራዎች ዕቅድ ዝግጅትን ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡

፫ ኮሌጁ ለተማሪዎች የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ያደራጃል፣ ይመራል፣ የሚሻሻሉበትን መንገድ ይቀይሳል፡፡

፬ የትምህርትና ሥልጠናውን ሂደት ለማዳበር አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችና አገልግሎቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡

፭ አጠቃላይ የአስተዳደር ሥራና ልማት የሚጐለ ብትበትን ዕቅድ ያዘጋጃል ፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

፮ በኤጀንሲው፣ በዲኑ ወይም በአካዳሚክ ኮሚሽኑ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

፲፮. የየኮሌጁ አካዳሚክ ኮሚሽን አደረጃጀት

፩ አካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ዲኑ -------------------------------- ሰብሳቢ፣

ለ/ የአካዳሚክ፣ የሥልጠናና የምርምር ምክትል ዲን --------------- አባል፣

ሐ/ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን -- አባል፣

መ/ የምርምርና ሕትመት ጽህፈት ቤት ኃላፊ - -------- አባል

ሠ/ የተከታታይ ትምህርት ሥልጠና ክፍል ኃላፊ-------------------------- አባል፣

ረ/ የአካዳሚክና የሥልጠና ዲፖርትመንቶች ኃላፊዎች------------------------ አባላት፣

1. direct and co-ordinate the administrative and financial activities of the College:
2. direct and co-ordinate the development activities plan of the College.
3. organize and direct the services provided to the students by the college, devise ways to improve them.
4. cause the provision of facilities and services necessary to develop the education and training process.
5. prepare plans aimed at enhancing the overall administrative and development activities of the College; and ensure their implementation upon approval.
6. perform other activities particularly assigned to him by the Agency, the Dean or the Academic Commission.

16. ***Organization of the Academic Commission of Each College***

1. The Academic Commission shall have the following Members:

   (a) The Dean ………………….Chairperson;

   (b) The Academic, Training and Research Deputy- Dean ………………Member;

   (c) The Administration and Development Deputy -Dean……………….Member;

   (d) The Head of the Research and Publication Office ………………………Member;

   (e) The Head of the Continuing Education Training Department ….. Member;

   (f) The Heads of Academic and Training Departments ……………Members;

ሰ/ የሬጅስትራር ጽህፈት ቤት ኃላፊ------ አባል፣

ሸ/ በኮሌጁ የአካዳሚክ ሠራተኞች የሚመረጡ ፫/ሶስት/ የኮሌጁ መምህራን --------- አባላት፣

ቀ/ የኮሌጁ መደበኛ ተማሪዎች መማክርት ሰብሳቢ እና አንድ የሴት ተማሪ ተወካይ ------- አባል

በ/ የሴት አሠልጣኝ ተወካይ --------- አባል።

፪ አካዳሚክ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ሸ/ ከተጠቀሱት አባላት መካከል የሚመረጥ አንድ ፀሐፊ ይኖረዋል።

፫ የአካዳሚክ ኮሚሽኑ አባላት ስብጥርና ብዛት እንደአስፈላጊነቱ እየታየ በኤጀንሲው ውሣኔ ሊለወጥ ይችላል።

**፲፯. የአካዳሚክ ኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር**

**አካዳሚክ ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለዲኑ ሆኖ፣ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦**

፩ የኮሌጁን የትምህርት ካላንደር መርምሮ ያፀድቃል።

፪ በኮሌጁ ዕቅድ ላይ ይወያያል፣ያዳብራል።

፫ የተለያዩ የትምህርትና የሥልጠና፣ የጥናት፣ የምርምርና የማማከር ፕሮግራሞችን የሚያሻሽሉና የሚያበለጽጉ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችሉ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም አተገባበራቸውን ይከታተላል።

፬ በኤጀንሲው የሚወጡ ሌሎች የአካዳሚክ መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል።

፭ ለትምህርትና ሥልጠናው ሂደት መሻሻልና መዳበር የተለያዩ ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ይጥራል።



(g) Head of the registrar Office … Member;

(h) Three staff members elected by the Academic Staff of the College .. Members;

(i) The Chairperson of the Council of regular students of the College and female trainees representative --------Members; and

(j) Women trainers' representative…member

2. The Academic Commission shall have a secretary elected from the members mentioned under sub-article 1(h) of this Article.

3. The composition and number of the members of the Academic commission may be changed by the decision of the Agency as may be necessary.

**17. *Powers and functions of the Commission***

**The Commission, being accountable to the Dean, shall have the following powers and function:-**

1. examine and approve the academic calendar of the College.

2. deliberate and enrich the plans of the college.

3. prepare guidelines that would enable to take measures to improve and enrich the various education and training, study, research and consultancy programs; and follow up their implementation upon approval.

4. follow up the implementation of other academic guidelines issued by the Agency.

5. design different methods for improving and developing the education and training process; and it shall strive for their implementation.

www.chilot.me

፮ የፌዴራል መንግሥቱን የከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የሠልጣኞችን የፈተና ማለፊያ መስፈርት ያወጣል፣በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፡፡

፯ ሠልጣኞች የሚመረቁበትን ነጥብና የምሥክር ወረቀት የሚያገኙበትን ሁኔታ በመመሪያው መሠረት ይወስናል፡፡

፰ የሠልጣኞችን ምረቃ መርምሮ ያፀድቃል፡፡

፱ ለሥልጠናና ለተለያዩ ጉዳዮች የሚከፈለውን የአገልግሎት ዋጋ አጥንቶ ለኤጀንሲ ያቀርባል፡፡

፲ ኮሌጁ ከተለያዩ ተቋሞች ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት እንዲጠናከር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

፲፩ ሌክቸረርነትና ከዚያ በላይ ያሉ የአካዳሚክ ማዕረጎች ይሰጡ ዘንድ በመምህራን የደረጃ ዕድገት ደንብ መሠረት ለቦርዱ አስተያየት ያቀርባል፡፡ ሆኖም ሌሎች የአካዳሚክ እድገቶችን ራሱ ይሰጣል፡፡

፲፪ የመማር ማስተማርንና የሥልጠናውን ሂደት ለማሻሻል በአስተዳደሩ አካላት የሚቀርቡ የጥናት ዕቅዶችን መርምሮ ያፀድቃል፣ ውጤቱንም በመገምገምና በማሳተም ለሚመለከታቸው አካላት እንዲሠራጩ ያደርጋል፡፡

፲፫ የኮሌጁን ሠልጣኞች አቀባበል፣ አመዳደብ፣ የትምህርት ደረጃ አወሳሰን፣ የዲስፕሊን ጉዳዮችንና ምረቃን የሚመለከቱ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ ለኤጀንሲው ያቀርባል ሲጸድቁም በሥራ ላይ ያውላል፡፡

፲፬ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፣

፲፭ በዲኑ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፲፰. የየኮሌጁ የአካዳሚክና ሥልጠና የዲፓርትመንት ካውንስሎች አደረጃጀት

፩ እያንዳንዱ አካዳሚክና ሥልጠና ዲፓርትመንት የዲፓርትመንት ካውንስል ይኖረዋል፡፡

፪ እያንዳንዱ ካውንስል የአካዳሚክ ሥልጠና ዲፓርትመንቱን ቋሚ የአካዳሚክ ሠራተኞች በሙሉ ይይዛል፡፡ የዲፓርትመንቱ ኃላፊ የካውንስሉ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

6. determine and control the implementation of the promotion criteria of trainees based on the higher Education and Technical and Vocational Training guidelines of the Federal Government.

7. determine the conditions for grade points for the graduation of trainees and awarding certificate in line with the guidelines.

8. examine and approve the graduation of trainees;

9. study and refer to the Agency service charges payable for training and other matters.

10. facilitate the condition for the strengthening of the relationships the College establishes with other institutions.

11. submit proposals to the board about Lectureship and other academic titles higher than this title would be awarded according to the Teachers Career Structure. It shall, however, award other academic promotions on its own.

12. examine and approve study proposal recommended by government bodies to improve the teaching learning and the training processes. It shall also evaluate, publish and distribute the findings thereof to the concerned bodies.

13. prepare and refer to the Agency criteria for the admission, assignment, determination of academic grade points, disciplinary matters and graduation of trainees; and implement the same upon approval.

14. issue its own meeting procedure.

15. carry out other activities assigned to it by the dean.

**18. *Organization of Academic and Training Department Councils of Each College***

1. Each Academic and Training Department shall have a Department council

2. Each Department council shall comprise, as members, all permanent Academic Staff of the Academic and Training Department and shall be presided by the Head of the Department.

፫ እያንዳንዱ የዲፖርትመንት ካውንስል ተጠሪነቱ እንደየአግባቡ ለዲኑ ወይም ለአካዳሚክ ሥልጠናና ምርምር ምክትል ዲኑ ይሆናል፡፡

**፲፱. የዲፖርትመንት ካውንስል ሥልጣንና ተግባር እያንዳንዱ ዲፓርትመንት ካውንስል**

፩ በአካዳሚክና ሥልጠና ዲፖርትመንት የሚሰጠውን የትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራም የጊዜ ሠሌዳ አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡

፪ የትምህርትና ሥልጠና ዘዴው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

፫ ወደ አካዳሚክና ሥልጠና ዲፖርትመንቱ የሚደለደሉትን ሠልጣኞች በሚመለከት ለአካዳሚክ፣ ሥልጠናና ምርምር ምክትል ዲን ሀሳብ ያቀርባል፡፡

፬ በአካዳሚክና ሥልጠና ዲፖርትመንቱ ውስጥ የሚሰጡትን ፈተናዎች ይቆጣጠራል፣ የፈተና ውጤቶችንም ለሬጅስትራር ጽህፈት ቤት መድረሳቸውን ይከታተላል፡፡

፭ የአካዳሚክና ሥልጠና ዲፖርትመንቱን የሚመለከቱ የአካዳሚክ ችግሮች የሚፈቱበትን ስልት በመቀየስ ያቀርባል፡፡

፮ የአካዳሚክና ሥልጠና ዲፖርትመንቱን በሚመለከቱ የአካዳሚክ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፡፡

፯ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፡፡

፰ የአካዳሚክና ሥልጠና ዲፖርትመንቱን ዝርዝር ዕቅድ አዘጋጅቶ ለአካዳሚክ፣ ሥልጠናና ምርምር ምክትል ዲን ያቀርባል፡፡

፱ አካዳሚክና ሥልጠና ሠራተኞችን ግምገማ በየሴሚስተሩ መጨረሻ ላይ ያካሂዳል፡፡

፲ በዲኑ ወይም በአካዳሚክ ሥልጠናና ምርምር ምክትል ዲን የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡



3. Each Department Council shall be accountable either to the Dean or to the Academic, Training and Research Deputy -Dean, as the case may be.

***19. Powers and functions of Department Council Each Department council shall:-***

1. prepare and submit time-table for the education and training offered by the respective Academic and Training Department.
2. submit proposal to improve the education and training method.
3. submit proposal of the Academic, Training and Research Deputy -Dean regarding the assignment of trainees to the respective Academic and Training Department.
4. supervise examinations being offered by the respective Academic and Training Department and shall follow-up the transfer of results to the Registrar office of the College.
5. devise and propose strategies on which the problems of the respective Academic and Training Department are alleniated.
6. give its opinions on other academic matters concerning the respective Academic and Training Department.
7. issue directive on its own meeting procedure;
8. prepare and submit the detailed plan of the respective Academic and Training Department. to the Deputy-Dean of Academic, Training and Research.
9. conduct the evaluation of the respective Academic and Training staff at the end of every semester.
10. carry out other activities assigned to it either by the Dean or by the Academic Training and Research Deputy-Dean.

www.chilot.me

**፳. ስለሌሎች የየኮሌጁ የበታች አመራር አካላት**

የእያንዳንዱ ኮሌጅ ልዩ ልዩ የአካዳሚክ፣ ሥልጠናና የምርምር ሥራ ክፍል ኃላፊዎች አመዳደብና አሠራር ኤጀንሲው በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ይወሰናል።

**ክፍል አምስት**

**ኮሌጅን በተለይ የሚመለከት የፋይናንስ ሥልጣን**

**፳፩. ስለኮሌጅ የፋይናንስ ነፃነት**

እያንዳንዱ ኮሌጅ ውሥጣዊ የፋይናንስ ነፃነት ይኖረዋል።

**፳፪. የኮሌጅ የገንዘብ ምንጭ**

የእያንዳንዱ ኮሌጅ የገቢ ምንጭ:-

፩ በአስተዳደሩ ከሚመደብ ዓመታዊ በጀትና ድጎማ

፪ ከሠልጣኞች ከሚሰበሰብ የሥልጠና ክፍያ፣

፫ ከኮሌጁ የውስጥ ገቢ፣

፬ ኮሌጁ ከሚያገኘው ሥጦታና ድጋፍ የሚውጣጣ ይሆናል።

**፳፫. ገቢ የማመንጨትና የመጠቀም መብት**

፩ ማንኛውም ኮሌጅ በጥናት ላይ የተመሰረቱ የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎችን ማካሄድና በገቢው የመጠቀም መብት አለው።

፪ አግባብ ባለው ህግ በሌላ አኳኋን የተደነገገው ቢኖርም እያንዳንዱ ኮሌጅ ከገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች የሚያገኘውን ገቢ ሥራ ላይ ማዋልና ተራፊውንም በየዓመቱ ፊሰስ ሣያደርግ መጠቀም ይችላል።

፫ በዚህ ክፍል አምስት የፋይናንስ ሥልጣን የተሰጠው እያንዳንዱ ኮሌጅ ገንዘብ፣ ንብረትና ሠራተኞች ግልፅነትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ይተዳደራል።



**20. *Other Lower Management Organs of each college.***

The assignment and functions of heads of the various academic, training and research activities of each College shall be determined by guidelines issued by the Agency

***Part Five***

***Fiscal Powers Particular to Colleges***

**21. *Financial Autonomy of College***

Every College shall have Internal Financial Autonomy.

**22. *Source of Fund of College***

The source of fund of each College shall be Derived from:-

1. Annual budget and subsidy to be allocated by the Government;
2. Tuition fee to be collected from the trainees;
3. The college's internal incomes; and
4. Donations and assistance the College may receive.

**23. *Right to generate and utilize income***

1. Each college shall have the right to undertake study - based, income generating activities and utilize any income therefore.
2. Without prejudice to any law prescribing otherwise, each College shall have the right to utilize the incomes it generates and utilize any residue of such income beyond a fiscal year.
3. The funds, property and employees of each College, to which the financial autonomy provided under this part five applies, shall be administered in a manner ensuring transparency and accountability.

**፳፬ የሂሣብ መዝገብ**

፩ የሂሣብ መዝገብ አያያዝን በተመለከተ በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ኮሌጅ የሂሣብ መዛግብቱን ከደጋፊ ሠነዶች ጋር በትክክልና በተሟላ መልኩ መያዝ አለበት::

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተመለከተው ጠቅላላ ድንጋጌ እንዳለ ሆኖ እያንዳንዱ ኮሌጅ

ሀ/ ማንኛውንም የኮሌጁን ገቢና ምንጮቹን

ለ/ የኮሌጁን ወጪዎች

ሐ/ የሂሣብ ሚዛንና የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ መዝገቦች መያዝ አለበት::

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ለተደነገገው ግዴታ አፈፃፀም ሲባል የኮሌጁ የበጀት ዓመት የአስተዳደሩን የበጀት ዓመት የተከተለ ይሆናል::

**፳፭. ስለኦዲት ሪፖርት**

፩ እያንዳንዱ ኮሌጅ የሂሣብ መዛግብትንና ገንዘብ ነክ ጉዳዮቹን በየዓመቱ በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማስመርመር አለበት::

፪ የኦዲተሩ የምርመራ ሪፖርት ለኤጀንሲው መቅረብ አለበት::

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፮ የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**

፩ በውል ወይም በሌላ ህግ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 (1) (ሀ) እስከ (ሠ) በተመለከተው መሠረት እንደገና የተቋቋሙት አምስቱ ኮሌጆች ያሏቸውን መብትና ግዴታዎች እንደያዙ ይቀጥላሉ::

24. ***Financial Records***

1. Without prejudice to the provisions of any other law, each college shall keep accurate and complete financial accounts and supporting documents.

2. Without prejudice to the provision of sub Article (1) of this Article , each college shall register and keep:-
   a) any incomes of the college and their sources;
   b) expenditures of the college
   c) balance sheet and cash flow statements

3. Regarding the implementation of the obligation provided for under sub Article (2) of this Article, the Fiscal Year of the college shall conform to the Fiscal Year of the Government.

25. ***Audit Report***

1. Each college shall investigate that its books of accounts and financial documents are audited annually by the Office of the City Cheif Auditor.

2. The audit report shall be presented to the Agency.

## PART SIX

## MISCELANEOUS PROVISIONS

26. ***Transfer of Rights and Obligations***

1. Without prejudice to contract or other laws, the Colleges that are Re-established According to Article 3 (1) (a) - (e) of this Proclamation shall continue exercising the Rights and obligations that they have acquired, respectively.

www.chilot.me

፪ የአቃቂ መካከለኛ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ለአቃቂ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ተላልፈዋል፡፡

**፳፯. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

፩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፳፪/፲፱፻፺፰ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፰. ደንብ እና መመሪያ የማዉጣት ስልጣን**

፩ ካቢኔዉ ለዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪ ካቢኔዉ የሚያወጣዉን ደንብ ለማስፈፀም ኤጀንሲዉ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

የካቲት ፬ ቀን ፪ሺ፩

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት



2. Rights and obligations of Akaki Medium Technical and Vocational Education and Training Institute are hereby transferred to the Akaki Technical and vocational, Education and Training College newly established by this Proclamation .

**27. *Repealed and Inapplicable Laws***

1. The Addis Ababa City Government Technical And Vocational Education and Training Collages establishment Regulations No 22/2006 is hereby repealed.
2. Any Proclamation, Regulation, directive or practice which are inconsistent with this Proclamation shall not apply to matters provided for in this Proclamation .

**28. *Power to issue Regulation and Directive***

1. The Cabinet may issue regulation to implement this Proclamation.
2. The Agency may issue Directive to implement the regulation which will be issued by the Cabinet.

**29. *Effective Date***

This Proclamation shall enter into force as of the *11th* day of February 2009.

***Done at Addis Ababa,***

***This February 11th Day of 2009***

***Addis Ababa City Council***